የፌዴራል ፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሰልጠና ማዕከል

የመጨረሻ ፍርድን የማረም ሥርዓት (ሰበር)

ስቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

የፌዴሬሽኑ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ

ሚያዝያ 2000

የመጨረሻ ፍርድን የማረም ሥርዓት (ሰበር)

የሰበር ሥርዓት ምንነት፣ ስለፈጣጊነቱና ሚናው

ሰበር የሚለው ቃል በእንግሊዘኛው ‘Cassation” በፈረንሳይኛው ደግሞ ‘Cassare’ የሚለውን ቃል የሚተካ ሲሆን ግርድፍ ትርጉሙም በየደረጃው ሥልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች ታይቶ የተሰጠን የመጨረሻ ፍርድ ውድቅ ማድረግ ወይም ደግሞ የተፈፃሚነቱን ኃይል ማስቀረት ማለት ነው፡፡

የሰበር ሥርዓት የሥልጣን ክፍፍልን መሠረት ያደረገን የመንግሥት አደረጃጀት ተከትሎ የተከሰተ ሲሆን ዓላማውም የሥልጣን ክፍፍልን መርህ በአግባቡ በተግባር ማዋል እንዲቻል ያለመ እንደነበር ከፈረንሳይ የህግ ሥርዓት ታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡ ይኸውም በህግ አተረጓጐም ሽፋን የህግ ተርጓሚው አካል የህግ አውጪውን የሥልጣን ወሰን ት ብ ዊ ለማድረግ ታስቦ የተዘረጋ ሥርዓት ነበር፡፡ በሌላ አገላለጽ ዜጐች በዳኞች ፈቃድና ፍላጐት ሳይሆን በወኪሎቻቸው በህግ አውጪው አማካኝነት በወጡት ህጐች መሠረት በፍ/ቤቶች የመዳኘት መሠረታዊ መብት አላቸው የሚለውን መርህ ተከትሎ ህግ ተርጓሚው በትርጉም ሥራ ሰበብ የህግ ማውጣት ተግባር እንዲያከናውን ለማድረግ ሲባል የተቀየሰ ስልት ሲሆን ይህ በሰበር የመጨረሻ ፍርድን እንደገና የማረም ተግባር በሂደት አድማሱን እያሰፋ በመሄድ በአንድ አገር ወጥ የሆነ የህግ አተረጓጐም እና አፈፃፀም መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ሆኗል፡፡

በየፍርድ ቤቶች በተሰጠ የመጨረሻ ፍርድ ላይ የተፈፀመን የህግ ስህተት በዚህ የመጨረሻ የዳኝነት ተቋም እንዲታረም የማድረግ ሥርዓት ህግ ተርጓሚው በውስጣዊ አደረጃጀቱ እራሱን በእራሱ ለመቆጣጠር የሚያስችልበት ሥርዓት ከመሆኑም ባሻገር በይዘታቸው በአግባቡ ያልታዩና በተገቢው መንገድ ያልተቀረፁ ህጎች መኖራቸውን በመመርመርና በማሳየት የህግ አውጪውን ትኩረት በመሳብ ፍትሐዊ እና ግልጽ የሆኑ ህጐች ተስተካክለው እንደወጡና እንዲቀረፁ ለማድረግ ስለሚረዳ በተዘዋዋሪ መንገድ

ቢሆን ህግ ተርጓሚው ህግ አውጪውን የሚቆጣጠርበት መንገድም ነው ማለት ይቻላል።

በአንድ አገር የህግ ሥርዓት የሰበር ተቋም የሚጫወተውን ሚና ከህግ የበላይነት መርህ ጋር ተያይዞ የሚታይ ነው። ልማት፣ ዲሞክራሲያ፣ ሠላምና ፀጥታ የዕድገት መሠረት መሆቸው እና በህግ የበላይነትና በእነዚህ የዕድገት ምሶሶዎች መካከል ጉልህ የሆነ ቁርኝት እንዳለ በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ። ፍ/ቤቶችም የህግ የበላይነትን በማንገስ ረገድ ቁልፍ ሥፍራ አላቸው። ሆኖም ፍ/ቤቶች የህግ የበላይነትን ሊያስከብሩ የሚችሉት የዜጎችን አመኔታ ያተረፉ እና ውጤታማ መሆናቸው የተረጋገጠ እንደሆነ ነው። ውጤታማ ናቸው የህዝብን አመኔታ አትርፈዋል ለማለት ደግሞ አስፈላጊ መለኪያዎች ሊሟሉ ይገባል። ይኸውም ፍ/ቤቶች ጥራት፣ ወጥነት ያለው ፍርድ ሲሰጡ እና ቀልጣፋ እና ተደራሽ በሆነ አኳኋን ሲደራጁ ነው። ጥራትና ወጥነት ያለው ፍርድ መስጠታቸው ከሚረጋገጥበት አንዱ በሰበር ችሎት ወይም በሰበር ፍ/ቤት የሚደረገው ዳኝነታዊ ቁጥጥር /legislative control/ አንዱ በመሆኑ የሰበር ሥርዓት ሚናው የላቀ ነው።

እንዲሁም የፍትሕ መሠረቱ ተመሳሳይ ጉዳዮችን በተመሳሳይ መንገድ /ዓይን/ ማየት ነው። በዳኝነት ሥልጣን ተዋረድ በመጨረሻው እርከን ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ ህጎች፣ ደንቦች፣ የህግ ፖሊሲዎች በበታች ፍ/ቤቶች በትክክልና ወጥነት ባለው ሁኔታ መተርጎማቸውንና መፈፀማቸውን ማረጋገጥ ቀዳሚ ግቡ በመሆኑ ዜጎች በህግ ፊት እኩል ናቸው የሚለውን ህገ-መንግሥታዊ መርህ በተግባር በማረጋገጥ ረገድ ህግ ተርጓሚው የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ለማድረግ የሚያስችለው ሥርዓት ነው።

ከላይ በተመለከተው ሁኔታ በኢትዮጵያ የህግ ሥርዓት የሰበር ተቋም አስፈላጊ መሆኑንና ሚናውን መጫወት ይችል ዘንድ በህገ መንግሥቱ በአንቀጽ 83 የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ቢኖረውም የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል በማለት በመደንገግ የሰበር ሥርዓቱን ዘርግቷል።

የአመቃቀሩ /የአደረጃጀቱ/ ስልት፡-

የሰበር ሥርዓት አደረጃጀት ከሀገር ሀገር ሊለያይ ይችላል፡፡ በፈረንሳይ፣ በጣሊያን፣ በቤልጂየም፣ በግሪክ የዳኝነት አካል አደረጃጀት እንደሚታየው እራሱን የቻለ የሥልጣን ደረጃ ያለውና በሰበር ለማረም ሲባል ብቻ የሰበር ፍ/ቤት (Court of Cassation) ሊቋቋም ይችላል፡፡ ይህ አይነቱ አደረጃጀት የሰበር ፍ/ቤት ከመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት እና ከይግባኝ ሰሚው (Court of appeal) ቀጥሎ በሦስተኛ የሥልጣን እርከን ላይ የሚገኝ ነው፡፡

በሌላ በኩል ለሰበር ሊቀርቡ የሚችሉትንና የማይችሉን ጉዳዮች ለመለየት የሚችል የተለየ የማጣሪያ ዘዴ እንዲኖረው በማድረግ ተመሳሳይ ተግባር እንዲያከናውን የአንድ አገር ጠቅላይ ፍ/ቤት አካል ሆኖ የተደራጀ የሰበር ሰሚ ክፍል (Cassation division) ሊደራጅ ይችላል፡፡ ለአብነት ያህል ኢስቶንያንና ግብጽን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያን የሰበር አደረጃጀት ስንመለከት በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 80(3) «<u>የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት</u> መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም <u>በሰበር ችሎት</u> የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡» በማለት መደንገጉና ይህንኑ ድንጋጌ ተከትሎም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 22(1) «አንድ ውሣኔ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 መሠረት <u>በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር</u> የሚሰማው አስቀድሞ ሦስት <u>የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞች የተሰየሙበት ችሎት</u> ውሣኔው ለሰበር የሚያበቃ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት ተብሎ ሲወሰን ነው» (ሰረዝ የተጨመረ) በሚል መደንገጉ የመጨረሻ ፍርድን እንደገና አይቶ የሚያርመው አካል እራሱን የቻለ የሥልጣን ደረጃ ይዞ የተደራጀ ሳይሆን በጠቅላይ ፍ/ቤት ሥር የሚገኝ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ አካል የሆነ ክፍል (division) ነው፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለመሆኑ በቅድሚያ በሦስት የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞች ታይቶ የተረጋገጠ እንደሆነ ብቻ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በማለት በዚሁ አዋጅ መደንገጉ ጉዳዩን በመለየት ረገድ የቅድሚያ ማጣሪያ ሥርዓት የተበጀለት መሆኑን ያመለክታል፡፡

በመሆኑም የሰበር ችሎት (cassation division) የዳኝነትን ተግባር አስመልክቶ ለጠቅላይ ፍ/ቤቱ ከተሰጡት ሥልጣኖች አንዱ መሆኑን እንጂ ከጠቅላይ ፍ/ቤት በላይ የሆነ እራሱን የቻለ እርከን ይዞ የተዋቀረ ተቋም አይደለም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርሰን ነው።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥልጣን

የኢትዮጵያ የሰበር አወቃቀር ጣምራ የፍ/ቤቶች ሥርዓት የያዘውን የፌዴራል መንግሥትን አደረጃጀት ተከትሎ የተዘረጋ ነው። ይህም በመሆኑ ሁለት ዓይነት የሰበር ሥርዓት ተቀምጧል።

ከዚህም በመነሳት በክልል ጉዳዩ የክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተመልክቶ የሰጠውንም ውሣኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር አይቶ የማረሙ ሥልጣን ህጋዊ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጥያቄ ይነሳል።

ለዚህም ጥያቄ ምክንያት የሆነው የሰበር ስልጣን ሰጪው ድንጋጌ ለትርጉም በር በሚከፍት አኳኋን በመቀረፁ ይመስላል።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥልጣን በፌዴራል ጉዳይ ላይ ብቻ የተገደበ ሊሆን ይገባል የሚለው አንደኛው የክርክር መስመር ሲሆን ሌላው ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥልጣን በዚህ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በክልል ጉዳይ በሰበር ተመልክተው የሰጧቸውና የመጨረሻ ፍርድ ይጠቃለላል የሚለው ነው።

የመጀመሪያው የክርክር መስመር በህገ-መንግሥቱ የተቀመጠውን ፌዴራላዊ የመንግሥትን አወቃቀር ምርኩዝ የሚያደርግ ነው ይኸውም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግሥትና በክልል መንግስታት የተዋቀረ ነው ክልሎች የየራሳቸው የህግ አውጪነት የህግ አስፈፃሚነትና የዳኝነት ሥልጣን አሏቸው። ለፌዴራል መንግሥቱ የተሰጠው ሥልጣን በክልሎች መከበር እንዳለበት ለክልሎች የተሰጠውን ሥልጣን በፌዴራል መንግሥቱ መከበር አለበት በማለት ህገ-መንግሥቱ የሥልጣን ወሰን አበጅቷል። የፍ/ቤቶች ጣምራነት ሥልጣን በሚለው አንቀጽ 80(2)

ላይ የክልል ጠ/ፍ/ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል ተብሎ የተደነገገውም ይህንን አወቃቀር ተከትሎ ነው።

ስለሆነም በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 80(3)(ሀ) «... መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሣኔ ...» የሚለው ሐረግ በጥቅል ደረጃ ለትርጉም በር በሚከፍት ሁኔታ የተቀመጠ ቢሆንም የመንግሥትን አወቃቀር በሚመለከተው ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ታይቶ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የፌዴራል ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ በሚል ሊተረጎም ይገባዋል። የክልልንም ጉዳይ እንደሚጨምር ተደርጉ ከተወሰደ ግን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትን የሰበር ሥልጣን የሰበር ሰበር ያስመስለዋል። ይህ ደግሞ ምክንያታዊ አይሆንም የሚለውን ነጥብ በማንሳት ነው።

ከዚህ ተቃራኒ የሆነው ደግሞ በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) (ሀ) « ... ማናቸውንም የመጨረሻ ውሣኔ ... » የሚለው ሐረግ ግልጽና የማያሻማ ነው በህግ አተረጓጎም መርህ መሠረት ህግ ግልጽ ሆኖ ከተገኘ የትርጉም ሥራ የማያስፈልገው በመሆኑ እንዳለ ሊወሰድ ይገባል።

ይኸው አገላለጽ አሻሚ ነው ትርጉም ያስፈልገዋል እንኳ ቢባል አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች እርስ በእርሳቸው አስተሳስረን በማየት ልንተረጉመው ይገባል። በአንቀጽ 80(2) «የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል» ብሎ ከደነገገ በኋላ በንዑስ አንቀጽ 3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ቢኖርም በማለት መደንገጉ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውንም ጉዳዮች ቢሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር ለማረም ሥልጣን ያለው መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ።

ምናልባትም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው ቢኖርም የሚለው የአንቀጽ 80(3) አነጋገር የጉዳዩ ባለቤት ማን ነው የሚለውን የሚከተል መሆኑን ስለሚያስረዳ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፌዴራል ጉዳይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ቢኖረውም በዚሁ ፍ/ቤት የተሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ በጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር

ሰሚው ችሎት ሊታይ የሚችል መሆኑን፤ በተመሳሳይ የክልል ጠ/ፍ/ቤት በክክል ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ቢኖረውም መሠረታዊ የህግ ስህተት ከተገኘ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት እንደገና ሊታይ የሚችል መሆኑን ለማመልከት የተቀመጠ አቀራረጽ ነው የሚል ትርጉም ሊነሳ ይችላል፡፡

ሆኖም ከላይ ከተመለከቱት ሁለት አይነት የህግ አተረጓጎም ዘዴዎች በተጨማሪ ህጉ አሻሚ ነው ከተባለ የህግ አውጪውን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ሊተረጎም ይገባዋል፡፡ የህግ አውጪው ሀሳብ ምን ነበር የሚለውንም የህገ-መንግሥቱ ጉባኤ ከያዛቸው ቃለ ጉባኤ (Minutes) መረዳት ይቻላል፡፡

የፍርድ ቤቶችን አወቃቀርና አደረጃጀት በተመለከተ የተዋቀረው ኮሚቴ ያዘጋጅው ንዑስ አንቀጽ የሰበር ሥልጣንን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ብቻ እንጂ ለክልል ጠ/ፍ/ቤቶች እንዳልሰጠና በኋላ ግን የሰበር ሥልጣን ለክልሎችም እንደሚያስፈልጋቸው በማየት እንደአሰፋፋው ከቁጥር 26-29 ገጽ 34-36 ያለው ቃለ ጉባኤ ስለሚያስረዳና

- በክልል ሰበር ሰሚ እንዲታይ ማድረጉ የጉዳዩ ብዛት ሊቀንስ ይችላል፡፡

- ክርክሮችንም በፍትሐዊነት መቋጨት ያስችላል፡፡
- በአገሪቱ ወጥ የሆነ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር ይረዳል የሚሉትን ነጥቦች መነሻ በማድረግ ምንም እንኳ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር ሥልጣኑ ተመልክቶ እንደገና ያየው ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር በፌዴራል ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይወሰን የክልልንም ጉዳይ በሰበር የማረም ሥልጣን ይኖረዋል በማለት በዚሁ ሰነድ ገጽ 43 ያስቀመጠ በመሆኑ፤ የህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80 አቀራረጽ ከላይ ለተነሳው ክርክር በር ከፍቷል ከሚባል በቀር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥልጣን በፌዴራል ጉዳይ ላይ ሳይወሰን የክልል ፍ/ቤቶች የሰጧቸውንም የመጨረሻ ውሣኔዎች በሰበር የማረም ሥልጣን ህገ-መንግሥታዊ መሠረት ያለው መሆኑን ያስረዳል የሚለው ነው፡፡

የሰበር ውሣኔ የስገዳጅነት ኃይል (ባህሬ)

የሰበር ሥርዓት ዋነኛ ሚና የህግ አተረጓጐም እና አፈፃፀም ወጥ እንዲሆንና ለተመሳሳይ ጉዳይ ተመሳሳይ ፍርድ መስጠት አለበት የሚለውን ደንብ እንዲተገበር ማድረግ ነው፡፡ (unifying the case law) የኮመን ሎው የህግ ሥርዓትም ሆነ የሲቪል ሎው የህግ ሥርዓት በዚህ የሰበር ሥርዓት ሚና ላይ በመርህ ደረጃ ልዩነት የላቸውም፡፡

በመጨረሻ ፍርድ ላይ የታየን የህግ ስህተት በሰበር እንዲታረም በማድረግ ወጥ የሆነ የህግ አተረጓጐምና አፈፃፀም እንዲሰፍን ማድረግ ነው የሚለው ሚና በሁለቱም የህግ ሥርዓቶች ተቀባይነት ያለው ቢሆንም ይህንኑ ዓላማ እንዴት ማሳካት ይቻላል በሚለው ላይ ግን ተመሳሳይ ስልት አይከተሉም፡፡

ኮመን ሎው የህግ ሥርዓት በመጨረሻው ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የመጨረሻና በበታች ፍ/ቤቶች የአስገዳጅነት ኃይል አለው (“Doctrine of Stare decisis”) የሚለውን መርህ የሚከተሉ ናቸው፡፡ ይህ ሥልት ፍርድን በመጨረሻ የማረም ተግባርን ዓላማ ቀጥተኛ ውጤት እንዲያገኝ በማስቻል ረገድ በጐ ጐኑ የጐላ ነው፡፡

በአብዛኛዎቹ የሲቪል ሥርዓት በሚከተሉ ሀገሮች ግን የሰበር ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ የሰጠው የህግ ትርጉም ውሣኔ ለተሰጠበት ጉዳይ ካልሆነ በቀር የአስገዳጅነት ኃይል የለውም፡፡ በእርግጥ እንደ ፈረንሳይና ቤልጂየም ባሉ ሀገሮች የበታች ፍ/ቤት የሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ በሰበር ፍ/ቤት ተሸሮ እንደገና እንዲታይ በተመለሰ ጊዜ የበታች ፍ/ቤቱ በዚህ የሰበር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ በሰጠው ውሣኔ የህግ ትርጉም ሳይገደድ የመሰለውን ውሣኔ መስጠት ይችላል፡፡ ነገር ግን የበታች ፍ/ቤቱ እንደገና እንዲያየው በተመለሰበት ጉዳይ ላይ ውሣኔ ከሰጠ እና የሰበር አቤቱታ ከቀረበ ጉዳዩ በሰበር ሙሉ ጉባኤ (full court) ወይም Assembly division ታይቶ ለሁለተኛ ጊዜ የሰበር ፍ/ቤቱ ውሣኔ ይሰጣል በዚህ እኳኋን ለሁለተኛ ጊዜ በሙሉ ጉባኤው የተሰጠውን ውሣኔ ለተነሳው ጉዳይ ብቻ የበታች ፍ/ቤቶች የሚገደዱበት በመሆኑ እጅግ በጠበበ ሁኔታ የሰበር ውሣኔን አስገዳጅነት ኃይል የዘረጉ መሆናቸው ሳይዘነጋ ነው፡፡ ከዚህ በቀር የሰበር ውሣኔ የአሳሪነት ውጤት ያለው አይደለም፡፡

የሰበር ፍ/ቤት በመጨረሻ በተሰጠ ፍርድ ላይ የተፈፀመን የህግ ስህተት በማረም ወጥ የሆነ የህግ አተረጓጐም እና አፈፃፀም እንዲሰፍን ማድረግ የሚችል ተቋም ነው ለሚለው አባባል መሠረት የሚያደርጉት በሀገራቸው ባሉት ሁሉም ፍ/ቤቶች የተሰጠን ፍርድ ለማረም የሚያስችል አንድ ሰበር ፍ/ቤት የመቋቋሙን እውነታ እና ይህ ፍ/ቤት የሚሰጠው የህግ ትርጉም የማሳመን ኃይሉ (persuasive power) የላቀ ነው የሚለውን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ በአስገዳጅነቱ የህግ ድጋፍ ሊኖረው አይገባም ለሚለው የሚሰጡት ምክንያት የአንድ ፍርድ የተፈፃሚነት ወሰን ፍርድ በተሰጠበት ጉዳይ ላይ ብቻ የሚወሰን እንጂ ከዚህ አልፎ ለሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ዳኞችም የቀረበላቸውን ጉዳይ ሲወስኑ ለውሣኔያቸው መሠረት የሚያደርጉት የህግ ትንታኔ በቀረበው ጉዳይ ላይ ብቻ ያተኮረ እንጂ ለወደፊትም ለሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ ተፈፃሚ ሊሆን በሚችል ጥቅል አገላለጽ መሆን አይኖርበትም፡፡ (Judges are forbidden to give regulatory judgment) የሚለው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሰበር ፍ/ቤት ውሣኔ ከበታች ፍ/ቤቶች የማሳመን ኃይል ከሚኖረው በቀር እንደ ህግ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል አይገባም፡፡ ህጉ በትክክል መተርጐሙን በማረጋገጥ ሂደት በቀረቡት ይግባኞች እና በሰበር ፍ/ቤቱ በተሰጠው የህግ ትርጉም ላይ ተመስርቶ የፍርድ ህግ “case law” ቀስ በቀስ እያደገ ሊሄድ ይገባል የሚለውን አስተሳሰብ ያራምዳሉ፡፡ ይህም በመሆኑ የ case law ዕድገት አዝጋሚ መሆኑንም ይጠቁማሉ፡፡

የአንድ ሀገር ህግ በትክክልና ወጥነት ባለው ሁኔታ በሁሉም ፍ/ቤቶች እንዲተረጐሙ በማድረግ በኩል የሰበር ሥርዓት ሚና (jurisprudence of the court) የላቀ መሆኑ ካላከራከረ ይህንኑ ሚና ተግባራዊ ለማድረግ የትኛው ስልት ውጤታማ ነው? ለምን?

ይህንኑ በተመለከተ የኢትዮጵያን ህግ ሥርዓት ስንመለከት፡-

በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3)(ሀ) «የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ በማለት ሥልጣኑን አስቀመጠ እንጂ በሰበር ሰሚነቱ ሥልጣን

የተሰጠው ውሣኔ የተፈፃሚነት ወሰን እስከምን እንደሆነ ገላጭ አይደለም፡፡ ዝርዝር ህጉ አዋጅ ቁጥር 25/88 ቢሆን ይህንኑ አብራርቶ አልደነገገም፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/88 በአንቀጽ 10 ላይ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠውን የሰበር ሥልጣን ባሻሻለው አዋጅ ቁጥር 454/97 «የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም በየትኛው ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡» በሚል ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም በሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሣኔ የተፈፃሚነት ወሰን ፍርድ ባረፈበት ጉዳይ ላይ ብቻ የተወሰነ ወይም ደግሞ በተሰጠው ትርጉም የማሳመን ኃይል የተነሳ ለሌሎች ፍ/ቤቶች እንዲከተሉት የተተወ ብቻ ሳይሆን ለተመሳሳይ ጉዳይ የአስገዳጅነት ኃይል እንዲኖረው ማድረግ መሆኑን ጭምር በግልጽና በማያሻማ መንገድ ተገልጿል፡፡

ይኸው ድንጋጌ ከህገ-መንግሥት አንቀጽ 34/5/፣ 78/5/ እና 80/3//ሀ/ «…. የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሣኔ …» በሚል ከተመለከተው ጋር ተገናዝቦ ከታየ የሰበር ሰሚው ውሣኔ የአስገዳጅነት ኃይል በማሻሻያ አዋጁ እንደተመለከተው በመደበኛ ፍ/ቤቶች ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይሆንም፡፡

ሆኖም የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የህግ ትርጉም የሚሰጥባቸው ጉዳዮች፡-

- ተግባራዊ ፋይዳ ባላቸው እና በፍ/ቤቶች የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ በሚያጋጥሙና የእነዚህን ፍ/ቤቶች ትኩረት በሚስቡ፣
- የህግ መፍትሄ በሚያስፈልጋቸው ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችና የህግ ትርጉም የሚሰጥባቸው ጉዳዮች በዘላቂነት ተፈፃሚነት ሊኖራቸው የሚችሉና በሥር ፍ/ቤቶች እንደ *ሥራ መመሪያ* (Yardstick) ሆኖ ማገልገል የሚችሉ ጉዳዮች መሆን እንደሚገባቸውና የሚሰጠውም የህግ ትርጉም ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥረት ተደርጉበት በተብራራ እና በበቂ የህግ ትንታኔ የተደገፈ መሆን

እንደሚገባው ድንጋጌው በእራሱ ጠቋሚ ነው ለማለት ይቻላል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሣኔዎች በየደረጃው ላሉ ፍ/ቤቶችና ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላት አሳትሞ ያሰራጫል የሚለው የዚሁ አዋጅ ድንጋጌ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው። ህግ ተርጓሚው የተሰጠውን ትርጉም የመለወጡ ሁኔታ በእራሱ የረዥም ሂደት የሚታይ ውጤት መሆኑ ቢታወቅም በውጫዊ ሁኔታዎች የተነሣ ሊለወጥ የሚችልበትም አጋጣሚ ይኖራል። ይኸውም የተሰጠው የህግ ትርጉም በሥራ ላይ ያለውን ህግ መሠረት ያደረገ አይደለም የህጉን መንፈስ አልተከተለም የተሳሳተ ነው የሚባል ከሆነ ይህንን አስመልክቶ በህግ ባለሙያዎች በሚሰጥ የህግ ትችት፣ ምርመራዊ አስተያየት መነሻ፣ እንዲሆም የበታች ፍ/ቤቶች በተሰጠው ትርጉም መመራት ያለባቸው ቢሆንም የተሰጠውን ትርጉም ለመቀበል የሚቸገሩበትን የህግ ምክንያት ካለ በእነሱ በኩል የሚነሳውን ክርክር (Resistance) መነሻ በማድረግ አስቀድሞ የተሰጠ የህግ ትርጉም የሚታረምበት መንገድ ይፈጠራል።

ይህም ብቻ ሳይሆን ቋሚ እንዲሆን ተፈልጐ በአንድ ወቅት የተሰጠ ትርጉም በህብረተሰቡ የሚታየውን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ቴክኖሎጂካል ለውጥ ተከትሎ ከእነዚሁ ለውጦች ጋር ሊጣጣም በሚይችል አኳኋን እንደገና ማየትንም ስለሚጠይቅ የህግ ትርጉም የሚለወጥበት መንገድም አለ።

ለዚህም ነው በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 ላይ ሆኖም የሰበር ችሎቱ በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ የተለየ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል በሚል መደንገግ ያስፈለገው።

ስለሰበር ችሎት የሚቀርቡትን ጉዳዮች የመለየት ተግባር

(Screening Mechanism)

የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓትን በሚመለከት በተደነገገው በአዋጅ ቁጥር 25/85 አንቀጽ 22(1) ላይ «... በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር የሚሰማው አስቀድሞ ሦስት የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞች የተሰየሙበት ችሎት ውሣኔው ለሰበር የሚያበቃ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት ብሎ ሲወሰን ነው።» በሚል የቅድሚያ ማጣሪያ ሥራ እንደሚያስፈልግ ተደንግጓል። በተገቢው ፍጥነት ከመስማት መብት አንፃር በዚህ

አካኋን ተጣርቶ ካልቀረበ ሰበር ሰሚው ችሎት የተሰጠበትን ከፍተኛ ኃላፊነቱ ለመወጣት ይሳነዋል፡፡ በሺ የሚቆጠሩ ጉዳዮችን በአፋጣኝ መርምሮ የመወሰን ተግባር በአገሪቱ ወጥ የሆነ የህግ አተረጓጐምና አፈፃፀም እንዲኖር ለማድረግ ካለመው ግብ ጋር አብሮ ሊሄድ የሚችል አይሆንም፡፡

በመስኩ የዳበረ ልምድ ባላት በፈረንሳይም የህግ ስህተት አለበት የተባለውን ፍርድ መርምሮ ወድቅ ለማድርግም ሆነ የሰበር አቤቱታውን ለመሰረዝ የእራሱ የሰበር ፍ/ቤቱ ሥልጣን ሆኖ ከላይ የተጠቀሰውን እንቅፋት ለማስቀረት ሲባል ጉዳዩ በቅድሚያ ልምድ ባካበቱ 3 ዳኞች ተመርምሮ ፍርዱ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑንና አለመሆኑን የሚለይበትን ሥርዓት ዘርግተዋል፡፡

እነዚህ ዳኞች ፍርዱን ተመልክተው የህግ ስህተት የለበትም የሚሉትን ውድቅ አድርገው በሰበር ሊታይ የሚገባውን ጉዳይ ብቻ በደንበኛው ሥርዓት በሰበር ፍ/ቤት እንዲታይ ያስተላልፋሉ፡፡ ይህም የማጣራት ሥርዓት ፈጣንና ያልተወሳሰበ፣ በጥሞና መመርመሩ እንዳለ ሆኖ ውድቅ ለማድረግ ምክንያት ማስፈር አስፈላጊ ባለመሆኑ እና የሰበር ፍ/ቤቱ አስፈላጊ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ ጊዜውን ከሚያጠፋ ይልቅ የፍርድ ህግን case law መፍጠር በሚያስፈልጋቸው የህግ ችግሮች ላይ አተኩሮ አስፈላጊ ሥራ እንዲሰራ በማድረግ ረገድ ጠቀሜታቸው የጎላ ነው፡፡

በተለቭም

- ከጉዳዮች ከባድነት ውስብስብነትና ቅለት
- የሕብረተሰብን በጠቅላላው የሚመለከት ወይም የፍርድ ውጤት በተከራካሪ ወገኖች ብቻ ተወስኖ የሚቀር መሆኑንና አለመሆኑን በሚሉትና በመሳሰሉት መስፈርቶች ላይ በጉዳዮች ላይ ልዩነት ሳይደረግ ሁሉም ጉዳይ የህግ ስህተት አለበት ከተባለ በተመሳሳይ የክርክር መስመር በተመሳሳይ ጊዜ እና ጉልበት የሚመረመር በመሆኑ የቅድመ ማጣሪያ ሥራ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በሰበር ፍ/ቤት ቀርበው ሊታዩ የሚችሉ መሆን አለመሆኑን መለያው የህግ ስህተት እንደመሆኑ በፍርዱ ላይ የህግ ስህተት አለበት ወይም የለበትም ለማለት አጋዥ የሚሆን መሪ ደንብ ወይም መስፈርት ያለመቀመጡ ጉዳይ የብዙ አገሮች የሰበር ሥርዓት እጥረት ነው ማለት ይቻላል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 22(1) እንደተመለከተውም ውሣኔው ምንም ይሁን ምን የመለያው መንገድ መሠረታዊ የህግ ስህተት ብቻ በመሆኑ ከላይ እንደታየው በጉዳዮች መካከል ልዩነት አላደረገም፡፡

በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3)(ሀ) «... መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውም የመጨረሻ ውሣኔ ...» በማለት በመደንገጉ የመለያ መስፈርቶች በፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት መኖርና ፍርዱም የመጨረሻ ሆኖ መገኘት ብቻ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ይህንኑ ህገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ በወጣው ዝርዝር ህግ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 22(1) በተመሳሳይ «... ውሣኔው ለሰበር የሚያበቃ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት ብሎ ሲወስን፡፡» በማለት ተገደበ እንጂ አጣሪ ዳኞችም ሆኑ ሰበር ሰሚው ችሎት ሊመሩ የሚችሉበትን ዝርዝር ሁኔታ አላስቀመጡም አጣሪ ዳኞች ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ መገናዘቢያ መንገድ ከመሆኑም ባሻገር ባለጉዳዮች በየትኛው ፍርድ ላይ የሰበር አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን ለማለየት ስለሚረዳ አስፈላጊነቱ አከራካሪ አይሆንም፡፡ በአንድ ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ምን ምን ሁኔታዎች ሲከሰቱ ነው? ለሚለው ጥያቄ አመላካች ሁኔታዎችን ለመጥቀስ ያህል፡-

- የተሳሳተ ህግን ለውሣኔ መሠረት ማድረግ
- ህግን አዛብቶ መተርጐም
- የህግ ጥሰት (breach or violation of the law)
- አግባብነት የሌለውን ህግ ጠቅሶ ለውሣኔ መሠረት ማድረግ
- የፍርድ አካሄዱ የተሟላ አለመሆን
- ለፍርድ መደምደሚያ የተሰጠው ትንታኔ በበቂ የህግ ምክንያት አለመደገፍ እና እርስ በእርሱ የተጋጨ ሆኖ መገኘቱ፣
- የሥልጣን አለመኖር ምንም እንኳ በአግባቡ ታይቶ የተወሰነ ቢሆንም ወይም እንደገና ማየቱ የውሣኔውን ውጤት ለማስለወጥ ቢያስችልም የፍርድ ትክክለኛነት እንደ መለኪያ ከወሰድን የተዛባ አሠራርን የሚጠፈጥር በመሆኑ፣
- ለሌላ አካል የተሰጠን ሥልጣን ተክቶ ማየት፣
- በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ፍርድ ሲሰጥ፣

- ያልተጠየቀ ዳኝነት ሲሰጥ fair- trail (adversarial principle) ጋር የተያያዘ በመሆኑ፣
- የተጠየቀ ዳኝነት ሲነፈግ
- ፍርድ ያላረፈበትን ጉዳይ ማስፈፀም የማለት ናቸው።

<u>የማስረጃ ምዘና</u>

ማስረጃው ይታመናል ወይስ አይታመንም? Credibility of evidence የሚለው ጉዳይ የሚየለው በዳኛው አእምሮ ወይም እንደዳኛው የሚወሰን በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞብናል ለማለት መነሻ ሊሆን የሚችል አይመስልም።

እንዲሁም ማስረጃው ክብደት አለው ወይስ የለውም የሚለው ጥያቄ አስቀድሞ በታየው የፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት የሚያበቃ መነሻ ሊሆን አይችልም የሚል ሀሳብ በአንድ በኩል ሲነሳ በሌላ በኩል ይኸው የዳኛ ሥራ የማስረጃ ህግ መሠረት ሊያደርግ ይገባዋል። ይኸውም በአንድ ጉዳይ የቀረበው ማስረጃ እንደ የጉዳዩ አይነት እየተለየ አስፈላጊ የሆነው የማስረጃ ክብደት መኖሩ ማረጋግጥ አለበት የፍ/ብሔር ጉዳይ ከሆነ ከሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች የተሻለ ማስረጃ ማን አቀረበ የሚለውን፤

የወንጀል ጉዳይ ከሆነም ወንጀል የተፈፀመ መሆኑን የዳኛውን አእምሮ ሊያሳምን የሚችል በቂ ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ እንዳለበት የማስረጃ ህግ መርህ ያስገነዝባል።

በመሆኑም የማስረጃውን አመዛዘን በሚመለከት ዳኛው በዚህ አኳኋን አይቶ መለካቱን ማረጋገጥ የግድ ይላል። በዚህ መለኪያ መሠረት ከማስረጃ ህግ አንፃር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑንና አለመሆኑ ታይቶ ሊመረመር ይገባል የሚለው ሀሳብ ሲቀርብ ይታያል።

ከዚህ ላይ ሳይነሳ የማይታለፈው ነገር ቢኖር ለሰበር የሚቀርቡ ጉዳዮችን አጣርቶ የማቅረቡ ተግባር በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊከናወን የሚገባው መሆኑ ነው። የሥልጣን ክፍፍል ሥርዓት በተዋቀረበት እንደ እኛ ሀገር ባለ የፍርድ ሂደት የዚህ አጣሪ ክፍል ቃል የመጨረሻ በመሆኑ የተዛባን ፍትሕ ሊታረም ወይም ሊስተካከል የሚችልበት

መንገድ ዝግ ያደርገዋል። በዚህም የተነሳ ፍትሕ እንደተጓደለ ይቀራል። የሰበር ችሎቱ የተቋቋመበትን ዓላማም ዋጋ ቢስ ያደርገዋል።

ሌላው የተሳሳተ ውሣኔ እንዲታረም ማድረግ በፍርድ በደል ደርሶብኛል የሚለው ወገን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የጠቅላላው ሕብረተሰብ ፍላጐትም ጭምር ነው። ይህም በመሆኑ በኮመን ሎውም ሆነ በሲቪል ሎው የህግ ሥርዓት ህግ በትክክል ተተርጉሞ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ መንግሥትንም የሚመለከት ጉዳይ ነው። እንደፈረንሳይ፣ ቤልጂየም እና ጣሊያን ባሉ ሀገሮች በሰበር ፍ/ቤት በሚካሄድ ክርክር ሂደት ዐ/ሕግ ተሳታፊ ነው። ተከራካሪ ወገኖች ባቀረቡት ክርክር ላይ አስተያየት ከመስጠት ጀምሮ የህግ ስህተቶች ይታረም ዘንድ በህግ ስም አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው።

የህጉ አተረጓጐም ወጥ መሆኑንና ትርጉሙም ከህጉ፣ ከህግ አውጪው ሀሳብ፣ ከህዝቡ ጥቅም እና የፐብሊክ ፖሊስ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ዐ/ሕግ የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ በተሰጠው ፍርድ ተሟጋቾች በፍርዱ ተስማምተው ለሰበር አቤቱታ ባያቀርቡም ፍርዱ የሚፈፀም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍ/ቤት አላግባብ ሥልጣኑን ተጠቅሟል (abuse of power by the court) በሚል መነሻ በህግ ስም የሰበር አቤቱታ የማቅረብ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 22(2) «ጉዳዩ በሰበር እንዲታይለት የሚፈለግ አቤቱታ አቅራቢ ...» በሚል ከመደንገጉ በቀር ዐ/ሕግ በህግ ስም (in the interest of the law) አቤቱታ ማቅረብ የሚችል መሆኑን ባይገልጽም የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጠናን ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/87 በአንቀጽ 8 ላይ የሕዝቡን እንዲሁም የፌዴራል መንግሥቱን መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በፌዴራልና በክልል ፍ/ቤቶች በማናቸውም ዳኝነት ሰሚ አካል ክስ እንዲመሰረት ያደርጋል ወይም ጣልቃ በመግባት ይከራከራል፤ በማለት ሥልጣኑ የተደነገገ በመሆኑ «አቤቱታ አቅራቢ ...» የሚለው ሀረግ ዐ/ሕግንም ሊጨምር ይችላል ወይስ አይጨምርም የሚለው ጥያቄ ሊነሳ ይችላል።

ማጠቃለያ

በሰበር አማካኝነት የተሰጠን ፍርድ እንደገና የማረም ሥርዓት በብዙ አገር የህግ ሥርዓቶች እውቅና ያገኘ፣ ጉዳይ ነው። ይህንንም የማረሚያ ሥርዓት በመዘርጋት ፍትሕ እንዲሰፍን፣ በህግ አተረጓጐም ረገድ ወጥነት እንዲኖርና ጉዳዮችን በተገቢው ፍጥነትና ወጥ እንዲቋጩ ለማድረግ አስችሏል።

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠውንና የሰበር ሥልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ፍርድ በማረም ፍትሕ ለተጓደለበት ወገን መፍትሄ ከመስጠት ባሻገር ተመሳሳይ ጉዳዮች በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲዳኙ በማድረግ ህጎች ወጥነት ባለው ሁኔታ እንዲተረጉሙና እንዲተገበሩ በማድረግ በኩል ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል።